የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ–ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 7
ADDIS ABABA–31st October, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፭/፲፱፻፺፭ ዓ·ም
የአካባቢ ጥበቃ አካላት ማቋቋሚያ
አዋጅ ............................................ ገጽ ፩ሺ፱፻፴፱

## CONTENTS

Proclamation No. 295/2002
Environmental Protection Organs Establishment
Proclamation ........................................ Page 1939

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፭/፲፱፻፺፭

## የአካባቢ ጥበቃ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ

በአንድ በኩል የአካባቢ ልማትና አያያዝ የሥራ እንቅስቃሴዎችን፣ በሌላ በኩል የአካባቢ ጥበቃ፣ ቁጥጥርና ክትትል ተግባራትን ለተለያዩ አካላት መስጠት የሥራ ኃላፊነቶች አለመጣጣምንና የሥራ ድግግሞሽን በማስወገድ በአካባቢያዊ ሀብቶች በዘላቂነት ለመጠቀም የሚረዳ በመሆኑ፣

በፌዴራልና በክልል የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤቶች መሀል የተቀናጀ፣ ነገር ግን የየቅሉ የሆነ ኃላፊነትን የሚያጠናክር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የአካባቢ ጥበቃ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፭/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· "ባለሥልጣን" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ መሠረት እንደገና የተቋቋመው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፣

## *PROCLAMATION NO. 295/2002*
## *A PROCLAMATION PROVIDED FOR THE ESTABLISHMENT OF ENVIRONMENTAL PROTECTION ORGANS*

WHEREAS, assigning responsibilities to separate organizations for environmental development and management activities on the one hand, and environmental protection, regulations and monitoring on the other is instrumental for the sustainable use of environmental resource, thereby avoiding possible conflicts of intrests and duplication of efforts;

WHERE AS, it has become necessary to establish a system that fosters coordinated but differentiated responsiblities among environmental protection agencies at federal and regional levels;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### *General*

1. *Short Title*·

This Proclamation may be cited as the "Environmental Protection organs Establishment proclamation No. 295/2002."

2. *Definition*

Unless the context requires otherwise, in this proclamation:

1) "Authority" means the Environmental Protection Authority re–established under Article 3 of this proclamation;

፪· "አግባብ ያለው መሥሪያ ቤት" ማለት ቃሉ የተጠቀሰበት ድንጋጌ በሚነካው ጉዳይ ላይ በሕግ የተሰጠ ኃላፊነት ያለው የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል ነው፤

፫· "አካባቢ" ማለት በመሬት፣ በከባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት፣ በውሃ ፣ በሕያዋን፣ በድምፅ በሽታ፣ በጣዕም፣ በማኅበራዊ ጉዳዮች እና በሥነ ውበት ሳይወሰን፣ በተፈጥሮአዊ ሁኔታቸው ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉ ያሉበት ቦታ፣ እንዲሁም መጠናቸውን ወይም ሁኔታቸውን ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ሕያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ ተስተጋብሮቶቻቸው ድምር ነው፤

፬· "የአካባቢ ጥበቃ አካላት" ማለት ባለሥልጣኑ፣ ምክር ቤቱና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ እና ፲፭ ድንጋጌዎች የተጠቀሱት የዘርፍ የአካባቢ አሃዶችና የክልል የአካባቢ መ/ቤቶች ናቸው፤

፭· "አደገኛ ነገር" ማለት በሰው ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ጠጣር፣ ፈሳሽ ወይም የጋዝነት ባህሪይ ያለው ነገር ወይም ተክል፣ እንስሳ ወይም ረቂቅ ሕዋስ ነው፤

፮· "ጥበቃ" ማለት የተፈጥሮ ባህርይ እንዳይናጋ በመጠበቅና የተፈጥሮ ሀብቶች ምንጭ አቅምን በማጎልበት፣ የአሁኑን ትውልድ ፍላጎት የማርካቱ ሂደት የመጪውን ትውልድ ዕድል ሳያሰናክል እንዲሚላ ማስቻል ነው፤

፯· "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፰· "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከቱት የአገሪቷ ክፍሎች ማለት ሲሆን፣ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

፱· "የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት" ማለት ለአካባቢና ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ወይም ቁጥጥር በክልሉ ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም የክልል የመንግሥት አካል ነው።

## ክፍል ሁለት

## የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን

፫· *መቋቋም*

፩· ባለሥልጣኑ ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።

፪· ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

፬· ዋና መሥሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፣ እንደአስፈላጊነቱም ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላሉ።

፭· የባለሥልጣኑ ዓላማ

የባለሥልጣኑ ዓላማ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች የሰውን በጎ ሁኔታ እና የአካባቢን ደኅንነት በዘላቂነት ሊያራምዱ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ ሥልቶችን ፣ ሕጎችንና ደረጃዎችን ማዘጋጀት እና ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከናወነውን ተግባር በግንባር ቀደምትነት መምራት ነው።

፮· የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩· በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉ የአካባቢ ደኅንነት ዓላማዎችና በአካባቢ ፖሊሲው የተመለከቱት መሠረታዊ መርሆዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ያስተባብራል፤

፪· አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች፣ ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላትና ከሕዝብ ጋር በመመካከር የአካባቢ ፖሊሲዎችን፣ ስልቶችንና ሕጎችን ያዘጋጃል፣ ይገመግማል፣ ያሻሽላል ወይም እንዲዘጋጁ ያስደርጋል፣ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

2) "Competent Agency" means any federal or regional government organ entrusted by law with a responsibility related to the subject specified in the provisions where the term is used;

3) "Environment" means the totality of all materials whether in their natural state or modified or changed by human, their external spaces and the interactions which affect their quality or quantity and the welfare of human or other living beings, including but not restricted to, land atmosphere, weather and climate, water, living things, sound, odor,taste, social factors, and aesthetics;

4) " Environmental Protection Organs" means the Authority, the Council, the Sectoral and Regional environmental units and agencies mentioned under Article 14 and 15 of this Proclamation;

5) "Hazardous substance" means any substance in the solid, liquid or gaseous state, or any plant, animal or microorganism that is injurious to human health or the environment;

6) "Protection" means sustaining of the essential characteristics of nature and enhancing the capactiy of the natural resource base with a view to safeguarding the interest of the present generations without compromising the opportunity for the future;

7) "Person" means any natural or juridical person;

8) "Region" means any of those parts of Ethiopia specified as Regions under Article 47(1) of the Constitution of the FederalDemocatic Republic of Ethioia and for the purpose of this Proclamation, includes the Addis Ababa and Dire Dawa Administrations;

9) "Regional Environmental Agency" means any regional government organ entrusted, by that Region, with a responsibility for the protection or regulation of the environment and natural resources.

## PART TWO

## *Environmental Protection Authority*

3. *Establishment*

1) The Authority is hereby re-established as an autonomous public institution of the Federal Government.

2) The Authority shall be accountable to the Prime Minister.

4. *Head Office*

The Head office of the Authority shall be in Addis Ababa and it may have branch offices as necessary.

5. Objective of the Authority

The objective of the Authority is to formulate policies, strategies, laws and standards, which foster social and economic development in a manner that enhance the welfare of humans and the safety of the environment sustainable, and to spearhead in ensuring the effectiveness of the process of their implementation.

6. *Powers and Duties of the Authority*

The Authority shall have the powers and duties to:

1) coordinate measures to ensure that the environmental objectives provided under the Constitution and the basic principles set out in the environmental Policy of Ethiopia are realized;

2) prepare, review and update, or as necessary, cause the preparation of environmental policies strategies and laws in consultation with the competent agencies, other concernred organs and the public at large and upon approval, monitor and enforce their implementation;

፫· አካባቢን ለመጠበቅና የተጎዳ አካባቢን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ፣ አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፤ እንደአስፈላጊነቱም የአቅም ግንባታዎች ድጋፍ ይሰጣል፤

፬· በመንግሥትም ሆነ በግል ፕሮጀክቶች፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ሥልቶች፣ ሕጎችና መርሐ ግብሮች ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

፭· የሥራ ፈቃድ የመስጠት፣ የመተግበር ወይም ክትትል የማድረግ ሥልጣን የፌዴራል መንግሥት የሆነባቸው ወይም ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ይገመግማል፤ ለፈቃድ ሰጪው አካል ውሳኔውን ያሳውቃል፤ እንደተገቢነቱም የትግበራው ይሁንታ ሲሰጥ በተመለከቱ ግዴታዎች መሠረት ፕሮጀክቶቹ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤

፮· አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመሆን በረሃማነትን ለመከላከል፣ የድርቅን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ መፍትሔዎችን ያዘጋጃል፤ ለአተገባበራቸውም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

፯· አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የአካባቢ ደረጃዎችን ይወስናል፣ መከበራቸውንም ያረጋግጣል፤

፰· አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር በዓለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች ድርድር ላይ ይሳተፋል፤ እንደተገቢነቱም ስምምነቶቹ እንዲፀድቁ ሃሳብ ያቀርባል፤ ወይም እንዲቀርብ ያስደርጋል፤

፱· አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍ የአካባቢ ውሎች ለመተግበር ተፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎችን፣ ስልቶችን፣ ሕጎችንና መርሐ ግብሮችን እንደሁኔታው ያዘጋጃል፣ ወይም እንዲዘጋጁ ሃሳብ ያመነጫል፣ አዘገጃጀታቸውን ያስተባብራል፣ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፲· አደገኛ ነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ ሀገር ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን፣ እንዲሁም ሕያዋንን በዘረመል ምሕንድስና መለወጥን፣ ልውጥ ወይም ባዕድ ሕያዋንን ወደ አገር ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን የሚመለከቱ የአካባቢ ደኅንነት ፖሊሲዎችንና ሕጎችን አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፣ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፲፩· በልማት ዕቅዶችና በኢንቨስትመንት መርሐ ግብሮች ውስጥ የሚካተቱ የአካባቢ የአዋጪነት ማስሊያ ቀመሮችንና የስሌት ሥርዓትን አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ እንደሁኔታውም በጥቅም የመዋላቸውን ሂደት ይከታተላል፤

፲፪· ዘላቂነት የጎደለው የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀምንና ልምድን፣ የአካባቢ ጉስቁልናን ወይም ብክለትን ለመከላከል በሚያስችሉ የመግቻ እርምጃዎች ወይም የማበረታቻ ዘዴዎች መጠቀምን በተመለከተ አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር ሃሣብ ያቀርባል፤

፲፫· አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓትን ይዘረጋል፤

፲፬· የአካባቢ ጥበቃ ምርምሮችን ያስተባብራል፤ ያበረታታል፤ እንደአስፈላጊነቱም ራሱ ያካሂዳል፤

፲፭· አግባብ ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የአካባቢ ጥበቃ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በፌዴራሉ ሥልጣን ሥር ወደሚገኝ ማንኛውም መሬት፣ ቅጥር ግቢ ወይም ሌላ ቦታ ይገባል፤ ኃላፊነቱን ለመወጣት ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ማንኛውንም ነገር ይፈትሻል፤ ናሙናዎችን ይወስዳል፤

፲፮· የሀገሪቱን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ በየወቅቱ እያዘጋጀ ለመንግሥትም ለሕዝብም እንዲደርስ ያደርጋል፤

3) liaise with competent agencies in the field of environmental protection and rehabilitation and support them in capacity development;

4) establish a system for environmental impact assessment of public and private projects, as well as social and economic development policies, strategies, laws, and programmes;

5) where projects are subject to federal licensing, execution or supervision or where they are likely to entail inter- regional impacts, review environmental impact study reports of such projects and notify its decision to the concerned licensing agency and, as may be appropriate, audit and regulate their implementation in accordance with the conditions set out during authorization;

6) in cooperation with competent agencies, carry out studies to combat desertification and/or mitigate the effects of drought and prepare corrective measures and create favourable conditions for their implementation ;

7) in consultation with the competent agencies, set environmental standards and ensure compliance with those standards;

8) in consultation with competent agencies, take part in the negotiations of international environmental agreements and, as appropriate, initiate or cause the initiation of a process of their ratification;

9) in consultation with the competent agencies, formulate, or initiate and coordinate the formulation of policies, strategies, laws and programs to implement international environmental agreements to which Ethiopia is a party; and upon approval, ensure their implementation;

10) in consultation with competent agencies, formulate environmental safety policies and laws on the production, importation, management and utilization of hazardous substances or wastes; as well as on the development of genetically modified organisms and the importation, handling and utilization of genetically modified and alien species, and upon approval, ensure their implementation;

11) in cooperation with the competent agencies, prepare or cause the preparation of environmental cost-benefit analysis formulate and an accounting system to be used in development plans and investment programs and, as the case may be, monitor their application;

12) in consultation with the competent agencies, propose incentives or disincentives to discourage practices that may hamper the sustainable use of natural resources or the prevention of environmental degradation or pollution;

13) in consultation with the competent agencies, establish an environmental information system that promotes efficiency in environmental data collection, management and use;

14) coordinate, promote and, as may be appropriate, carry out research on environmental protection;

15) in accordance with the provisions of the relevant laws, enter any land, premise or any other place that falls under the federal jurisdiction, inspect anything and take samples as deemed necessary with a view to discharging its duty and ascertaining compliance with environmental protection requirements;

16) prepare and avail to the government as well as the public a periodic report on the state of the environment of the country;

፲፯· መደበኛ ያልሆኑ የአካባቢ ትምህርት መርሐ ግብሮችን ያስፋፋል፣ ትምህርቱን ይሰጣል፣ አካባቢያዊ ጉዳዮችን በመደበኛ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ለማካተት አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ትብብር ያደርጋል፣

፲፰· የአካባቢ ጥበቃ የድርጊት ዕቅዶችንና ፕሮጀክቶችን ዝግጅት ያበረታታል ወይም ያግዛል፣ ለድርጊት ዕቅዶቹና ፕሮጀክቶቹ ማስፈጸሚያ የሚውሉ እገዛዎችን ያፈልጋል፣

፲፱· የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ተፈጻሚ ለማድረግ መመሪያ ዎችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

፳· የአካባቢ አያያዝን እና ጥበቃን ተቀዳሚ ዓላማው በማድረግ ለሚሠራ ማንኛውም ድርጅት ወይም ግለሰብ ምክር እንዲሁም የሚቻል ሲሆንና የአካባቢ ምክር ቤት ሲስማማበት የፋይናንስ እንዲሁም የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣

፳፩· የአካባቢ አያያዝን እና ጥበቃን በሚመለከት ለክልሎች ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፣

፳፪· አግባብ ያላቸው መሥሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅና በሌሎች የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከቱ ሕጎች የተጣሉባቸውን ኃላፊነቶች በሚወጡበት ሁኔታ ላይ ምክር ይሰጣል፣ እንደአስፈላጊነቱም እርምት ሊወሰድባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ የውሳኔ ሃሳብ ለመንግሥት ያቀርባል፣

፳፫· በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ድንገተኛ ሁኔታዎችን ለመቋቋም ስለሚወሰዱ አስፈላጊ እርምጃዎች መንግ ሥትን ያማክራል፣

፳፬· ተገቢ ሆኖ ሲታየው ከኃላፊነቶቹና ከተግባሮቹ በከፊል ለሌሎች መሥሪያ ቤቶች በውክልና ይሰጣል፣

፳፭· የንብረት ባለቤት ይሆናል ፣ ውል ይዋዋላል፣ ይከስሳል፣ ይከሰሳል፣ እንዲሁም

፳፮· ዓላማዎቹን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

፯· <u>የባለሥልጣኑ አቋም</u>

ባለሥልጣኑ፣

፩· የአካባቢ ምክር ቤት ከዚህ በኋላ «ምክር ቤቱ» እየተባለ የሚጠራ፣

፪· በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና አንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ እና

፫· አስፈላጊው ሠራተኞች

ይኖሩታል።

፰· <u>የምክር ቤቱ አባላት</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

ሀ) ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም በእርሱ የሚሰየም ሰብሳቢ፣

ለ) በፌዴራል መንግሥት የሚሰየሙ ............ አባላት፣

ሐ) ከእያንዳንዱ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሚሰየሙ........................... አባላት፣

መ) የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ተወካይ፣

ሠ) በአካባቢ አያያዝ የተሰማሩ ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካይ፣

ረ) የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ተወካይ፣ እና

ሰ) የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር።

፱· <u>የምክር ቤቱ ሥልጣን</u>

ምክር ቤቱ

፩· የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ ተግባራዊነትን በሚመለከት ባለሥልጣኑ በሚያቀርበው ዘገባ መሠረት ግምገማ ያካሂዳል፣ ተገቢውን ምክር ይሰጣል፣

፪· ተዘጋጅተው የሚቀርቡለትን የአካባቢ ፖሊሲዎች፣ ስልቶችና ሕጎች ይመረምራል፣ የውሳኔ ሃሳብ ለመንግሥት ያቀርባል፣

፫· ባለሥልጣኑ የሚያዘጋጃቸውን የአካባቢ ደረጃዎች እንዲሁም መመሪያዎች ይገመግማል፣ ያፀድቃል።

፲· <u>የምክር ቤቱ ስብሰባ</u>

፩· ምክር ቤቱ በስድስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣

17) promote and provide non-formal environmental education programs, and cooperate with the competent agencies with a view to integrating environmental concerns in the regular educational curricula;

18) promote or assist in the formulation of environmental protection action plans and projects and solicit support for such action plans and projects;

19) prepare directives to implement environmental protection laws and, upon approval, ensure their implementation;

20) advise and, as feasible and subject to the consent of the Environmental Council, provide financial as well as technical support to any organization or individual having as its objective the management and protection of the environment;

21) provide advice and support to regions regarding the management and protection of the environment;

22) provide advice to competent agencies regarding the discharge of their obligations under this Proclamation or under other laws pertaining to environmental protection and, as appropriate, give recommendations to the government regarding measures necessary to ensure compliance;

23) advise the Government on measures necessary to cope with environmental emergency situations;

24) delegate some of its powers and duties, as it may be deemed appropriate, to other agencies;

25) own property, enter into contracts and sue and be sued; and

26) carry out such other activities as are necessary for the fulfillment of its objectives.

7. *Organization of the Authority*

The Authority shall have:

1) an Environmental Council herein after referred to as the "Council".

2) a Director General and a Deputy Director General appointed by the Government; and

3) the necessary staffs.

8. *Members of the Council*

The Council shall have the following members:

(a) the Prime Minister or his designate (Chairman)

(b) members to be designated by the Federal Government.

(c) a representative designated by each National Regional State,

(d) a represetative of the Ethiopian Chamber of Commerce,

(e) a representative of local environmental non-governmental organizations, and

(f) a representative of the Confederation of Ethiopian Trade Unions, and

(g) The Director General of the Authority.

9. *Responsibilities of the Council*

The Council shall:

1) review proposed environmental policies, strategies, and laws, and issue recommendations to the government;

2) based on report submitted to it by the Authority, evaluate and provide appropriate advise on the implementation of the environmental policy of Ethiopia;

3) review and approve directives, guidelines and environmental standards prepared by the Authority.

10. *Meetings of the Council*

1) The Council shall hold its regular meetings once every six months, but it may also, at any time, hold extraordinary meetings whenever deemed necessary.

፪· በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ አብላጫ ቁጥር ያላቸው አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፣

፫· የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፣

፬· የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## ፲፩· ስለ ዋናው ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባሮች

፩· ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና የሥራ ኃላፊ በመሆን የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፣

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ) በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ) የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

መ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ መርሐ ግብር መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል፣

ረ) የባለሥልጣኑን የሥራ እንቅስቃሴ ዘገባ ያቀርባል።

፫· ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን፣ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ ለሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

## ፲፪· የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባራት

፩· ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ከዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጥ መመሪያ መሠረት፣

ሀ) የባለሥልጣኑን ተግባሮች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ይረዳል፣

ለ) በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል።

፪· ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ለዋና ዳይሬክተሩ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች ያከናውናል።

## ፲፫· በጀትና የሒሣብ መዛግብት

፩· የፌዴራል መንግሥት የባለሥልጣኑን በጀት ይመድባል።

፪· ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሣብ መዛግብት ይይዛል።

፫· የባለሥልጣኑ የሒሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ሌሎች ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## ክፍል ሦስት

## የዘርፍ፣ የአካባቢ አሀዶችና የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤቶች

## ፲፬· የዘርፍ የአካባቢ አሀዶች

እያንዳንዱ አግባብ ያለው መሥሪያ ቤት የሥራ እንቅስቃሴዎቹ ከዚህ አዋጅና ከሌሎች የአካባቢ ጥበቃ ግዴታዎች ጋር ተጣጥመው መካሄዳቸውን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለው የአካባቢ አሀድ በሥሩ ያቋቁማል ወይም ይሰይማል።

## ፲፭· ስለክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤቶች

፩· እያንዳንዱ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲና እንክብካቤ ስልት በመመስረትና በውሳኔ ሂደት ሕዝቡን በማሳተፍ፣

ሀ) የክልሉን የአካባቢ እንክብካቤ ስልት የሚያዘጋጅ፣ እንዲሁም የአተገባበር፣ የግምገማና የክለሳ ሥራዎችን የሚያስተባብር፣

ለ) የክልሉን የአካባቢ ሁኔታ ክትትል፣ ጥበቃና ቁጥጥር ተግባር የሚያከናውን፣

ራሱን የቻለ የአካባቢ መሥሪያ ቤት ያቋቁማል፤ ወይም ከነባር መሥሪያ ቤቶች መካከል አንዱን ለዚሁ ተግባር ይሰይማል።

2) There shall be a quorum when a simple majority of the members are present.

3) Decisions of the Council shall be passed by a majority vote and, in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4) Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may draw up its own rules of procedure.

11. *Powers and Duties of the Director General*

1) The Director General shall be the head of the Authority and, as such, shall direct and administer the activities of the Authority.

2) Without limiting the generality stated in Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

(a) exercise the powers and duties of the Authority specified in Article 6 of this Proclamation;

(b) employ and administer employees of the Authority in accordance with the federal civil service laws;

(c) prepare and, upon approval, implement the annual work programme and budget of the Authority.

(d) effect expenditure in accordance with the approved budget and work programme of the Authority;

(e) represent the Authority in all its dealings with third parties; and

(f) submit reports on the activities of the Authority.

3) The Director General may, to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Authority, delegate part of his powers and duties to the Deputy Director General, and to other officials and employees of the Authority.

12. *Powers and Duties of the Deputy Director General*

1) The Deputy Director General shall, in accordance with directives given by the Director General:

(a) support the Director General in planning, organizing, directing and coordinating the activities of the Authority;

(b) perform other activities directed by the Director General.

2) In the absence of the Director General carry out the powers and duties of the Director General.

13. *Budget and Books of Account*

1) The Federal Government shall allocate the budget of the Authority.

2) The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.

3) The Authority's books of accounts and financial documents shall be audited annually by the Auditor General or by other auditors designated by him.

## *PART THREE*

## *Sectoral and Regional Environmental Units and Agencies*

14. *Sectoral Environmental Units*

Every competent agency shall establish or deisgnate an environmental unit that shall be responsible for coordination and follow-up so that the activities of the competent agency are in harmony with this Proclamation and with other enviromental protection requirements.

15. *Regional Environmental Agencies*

1) Each national regional state shall establish an independent regional environmental agency or designate an existing agency that shall, based on the Ethiopian Environmental Policy and Conservation Strategy and ensuring public participation in the decision making process, be responsible for;

(a) coordinating the formulation, implementation, review and revision of regional conservation strategies, and,

(b) environmental monitoring, protection and regulation.

፪· የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤቶች የፌዴራል የአካባቢ ደረጃዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣሉ፤ እንደአስፈላጊነቱም ከፌደራሉ የጠበቁ ደረጃዎችን በማውጣት ሥራ ላይ ሊያውሉ ይችላሉ።

፫· የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤቶች የየክልላቸውን የአካባቢና የዘላቂ ልማት ሁኔታ በተመለከተ ዘገባ በማዘጋጀት ለባለሥልጣኑ ያቀርባሉ።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፮· የተሻሩ ሕጎች**

፩· የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፱/፲፱፻፹፯ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪· ከዚህ አዋጅ ጋር ተቃራኒ የሆኑ ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

**፲፯· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም·

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2) Regional environmental agencies shall ensure the implementation of federal environmental standards or, as may be appropriate, issue and implement their own no less stringent standards.

3) Regional environmental agencies shall prepare reports on the respective state of the environment and sustainable development of their respective states and submit them to the Authority.

## PART FOUR
## *Miscellaneous Provisions*

16 *Repealed Laws*

1) Environmental Protection Authority Establishment Proclamation No. 9/1995 is hereby repealed.
2) All laws inconsistent with this Proclamation are inapplicable regarding matters provided herein.

17. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 31st day of October, 2002.

Done at Addis Ababa, this 31st day of October, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA